# አካባቢን መበከልም ፀረ-ሰብእና ወንጀል ነው

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)* *ሚያዚያ ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*

የጦቢያ ሕዝብ በቅዬው የሚከናወነውን መልካምም ሆነ ክፉ ነገር የማወቅ እድሉ እየተዘጋ የራሱን ጉዳይ የሚሰማው በውጪ ሰዎች በኩል መሆን ከጀመረ ውሎ አድሯል። የወሎን ድርቅ ለአለም ሕዝብ ይፋ ያደረገውና ለኢትዮጵያውያንም በውል ያሳወቀው አበሻ ሳይሆን አንድ የእንግሊዝ ጋዜጠኛ እንደነበር ይነገራል። አሁንም አለም ድንበር የለሽ ለመሆን እየተቀራረበች በመጣችበት ዘመን ከንቱዎች የቋንቋ ድንበር እየፈጠሩ እርስ በርሱ እያናከሱ የሚፈጁትን ሕዝብ ቁጥር የሚነግሩን የውጭ አገር ዘጋቢዎች ናቸው።[1] በቅርቡም በቆቃ ሐይቅ ብክለት ምክንያት በውሃ ተጠቃሚ ከነበሩት ዜጎቻችን መካከል ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ እስከ አምስትና ስድስት ሰዎች መሞታቸውን የነገሩን የውጭ አገር ጋዜጠኞች ናቸው።[2] እነዚህ ሟች ዜጎች ግብር እየከፈሉ የሚያሽቀረቅሯቸው፤ በቆቃ ሐይቅ ዳር የቆዳ ምርቶችን እያመረቱና የውጪ ምንዛሪ እያስገኙ ጮማና ብርንዶ አብልተው በውስኪ የሚያራጯቸው፤ የቁንጣን በሽታ ሲይዛቸውም ወደ በለጸጉት አገሮች እየላኩ የሚያሳክሟቸው "አገረ-ገዥዎችና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴሮች" ነን ባዮችማ ከቆዳ ፋብሪካው ውጪ ቆቃ አካባቢ የተከበሩ ዜጎች መኖራቸውን የሚያውቁም አይመስሉ።

ቆቃ አካባቢ እየደረሰ ያለው እልቂት መንስኤ የውሃ አረንጓዴ (አልጌ) መሆኑን የነገሩን የጦቢያ ጠቢባን ሳይሆኑ ፕሮፌሰር ብርያን ሁዋይቶን የተባሉ የዱርሃም ዩኒቨርሲቲ ሳይንቲስት ናቸው። እኒህ የተከበሩ ፕሮፌሰር የቆቃ ሐይቅ የተበከለው ማይክሮሲስቲስ በሚባሉ የአልጌ አይነቶች እንደሆነ ሲናገሩ ስለሰማኋቸው ስለሁኔታው የበለጠ ለመረዳት የተለያዩ ጥያቄዎችን ጠይቂያቸው ነበር። እርሳቸውም በተባለው ውኃ ላይ ምንም አይነት ሳይንሳዊ ምርምር እንዳላደረጉ ነገሩኝ። አያይዘውም አስተያየታቸውን በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጡትም በሁኔታው ያዘኑና የተጨነቁ ሰዎች ስለእልቂቱ ስለነገሯቸውና ከዚያም አልፈው የውኃውን ፎቶግራፍ ስላሳዩአቸው ሙያዊ ምክራቸውን ለመለገስ እንደነበር ገለጹልኝ። ሳይንቲስቱ ካላቸው የረጅም ዘመን ልምድ ውሃውን ከበከሉት ተውሳኮች ውስጥ አንዱ ማይክሮሲስቲስ አልጌ ለመሆኑ ብዙም ጥርጥር የላቸውም። ያም ሆነ ይህ እንደዚህ አይነቱ አሰቃቂ የወገኖቻችን እልቂት ከራሳችን ተደብቆ፣ ወደ አረብ አገር ዘልቆ፤ ወደ እንግሊዝ አገር ተሻግሮ ወደ እኛ እስከሚመጣ ድረስ ምንም የምናውቀው ነገር አልነበረም። ይህ በራሱ ጦቢያውያን ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን የስሜት ህዋሳትና አእምሮአቸውን በአገራቸው እንደልፈለጉ መጠቀም አለመቻላቸውን ከማሳየት አልፎ የሰው ልጅ በአገራችን ምን ያህል እንደረከሰ የሚያስገነዝብም ነው።

በምእራቡ አለም እንኳን ሰውን የሚያህል ፍጡር ዶሮ ወይም ወፍ እንኳን በአካባቢ ብክለት ምክንያት ሲታመምና ሲሞት በፍጥነት የጤና ባለሙያዎችና ሳይንቲስቶች እንዲያውቁት ይደረግና በአስቸኳይ ምርምር ተደርጎ የበሽታው ምክንያት ይታወቃል። ወዲያውኑም የህመሙ መንስኤ መከላከያና መቆጣጠሪያ መንገዱ ይዘረጋል። የሰው ልጅ ከዶሮና ከወፍ አንሶ በሚገኝባት ጦቢያ ግን ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ከአንድ አልፎ አምስትና ስድስት ሰዎች እስከሚሞቱ፤ እንዲያውም የውጪ ጋዜጠኛ ዜናውን ቀራርሞ በውጪ ሬድዮኖችና ቴሌቪዥኖች እስከሚነግረን ምንም አናውቅም። የጦቢያ ጋዜጠኛ ስለአገሩ እንዳይጽፍ በየጊዜው ደንብ ይደነገግበታል። የአገሪቱ ሳንቲስትና የጤና ባለሙያዎችም ከቤተ- ሙከራቸው ውጪ ቆቃ፣ ባሌ፣ ጂኒጀንካ ወዘተ እያሉ ካወሩ የሚደርስባቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ታሪክ ሲያነሳው የሚኖረውን የአርባ ሁለቱን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች እጣ ፈንታና የአገሪቱን ክስረት ያስታውሷል። የድሃን ቆዳ እየገፈፉ በገዙት ሱፍ ተለብጠውና በከራባት ታንቀው ከአለም ባንክ፣ ከአለም ጤና ድርጅት፣ ከዩኒሴፍና ከሌሎችም "ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች" "ለሕዝብ ጤንነት ማሻሻያ" እያሉ እርጥባን ሲቀበሉ የሚውሉት የጤና ጥበቃ ሚኒስትሮች እንደዚሁም መላ የአፍሪካ አምባገነኖች ሳይቀር በጥሩ ለማኝነታቸው የሚተማመኑባቸው የጦቢያ ገዥዎችማ እንደዚህ አይነቱን እልቂት እየኮተኮቱ አሳድገው ለሌላ ጊዜ መለመኛ ሊጠቀሙበት ያሰቡ ይመስላል። "ችንክር በል ማንን ልቶጎዳ ነው!" አትበሉኝ እንጅ እንዲያው በኔ ሞት ልመናና እርጥባን እንዴት አድርጎ ነው አገርን የሚያሳድገው? በችጋራም ሕዝብ ስም እየለመኑ ወደ ሆድ ያስገቡትስ እንዴት ብሎ ነው ከሰውነት የሚዋሀደውና ጤና የሚሆነው? ያሳዝናል! ፈጣጣ-ለማኞች የኢትዮጵያን ሕዝብ በቁሙ ሳለም ሆነ ሞቶ እርጥባን እየለመኑ ይበሉበታል።

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሞተው በዚህ በያዝነው ክፍለ-ዘመን ሰው ሊገድሉ በማይገባቸው እንከኖች ነው። "ስንት እንጁ?" ብላችሁ ሊሰላ የማይችል ሂሳብ አትጠይቁኝ። ከዚህ በፊት በተለያዬ ጊዜ ለመግለጽ እንደሞከርኩት[3-5] በእኔ አመለካከት ስለኢትዮጵያ በአሐዝ መልክ የሚነገሩት ቀመሮች (statistics) ሁሉ የእውነትነት ባህሪ (scientific merit) የሌላቸው ከንቱ ውዳሴዎች ናቸው። የሕዝብ ቆጠራው እንደሚታወቀው ስለቆጠራው ጠቀሜታ ብዙም የማያውቁ ሰዎች በፈለጉት መንገድ የሚቀንሱት ወይም ከፍ የሚያደርጉት የቁማር ጨዋታ መሆኑ የሚታወቅ ይመስለኛል። በሰፊው የአገራችን ክፍል የልደትም ሆነ የሞት ካርድ አይታወቅም። በብዙዎች በጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የበሽታና የሞት ምክንያቶች አይመዘገቡም። ሌላው ሳይቀር በአስተዳደር በደል ምክንያት ሕዝብ ሲያልቅ የሙታኑን ቁጥር ሆነ ብለው ይቀንሱታል። ሁለት መቶ አምሳ ሰው ገለው እንደሆነ በአምስት እጅ ቀንሰው የጠፋው ህይወት ሐምሳ ብቻ ይሉና ያርፉታል። አስራ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ በርሃብ በመሰቃየት ላይ ከሆነ አራት ሚሊዮን ብቻ ነው ይሉና ስምንቱን ሚሊዮን ሰው ያልሆነ ፍጡር አድርገውት ቁጭ ይላሉ። ይህ ማለት እንግዲህ በነሱ ዘንድ የሰው ነፍስ በውስጣቸው የሌለ ሰዎች በአገራችን አሉ ማለት ነው።

አሳፋሪው የአፍሪካ ጤና ጉዳይ ግራ የገባቸው አንዳንድ ምእራባዊያን ሳይንቲስቶች ሳይቀር ይህንን እንቆቅልሽ መነጋገሪያ ካደረጉት ውለው አድረዋል። በአንድ ወቅት በአንድ ትልቅ የትምህርት ተቋም ውስጥ የአካባቢ ብክለትን ጨምሮ የሶስተኛው አለም የጤና ችግሮችን በሚዳስስ ጉባኤ ላይ ተሳትፌ ነበር። ስብሰባው ያነጣጠረው ዲዲቲ በሚባለው የወባ ማጥፊያ ኬሚካል ላይ ነበር። እንደሚታወቀው ዲዲቲ መሬት ላይ ካረፈ በኋላ ለአያሌ አመታት ሳይጠፋ አፍር ውስጥ ይኖራል። ይህ ዲዲቲ የሚባለው ኬሚካልም ካንሰር እንደሚያመጣ ተረጋግጧል። [6] ዲዲቲን በተመለከተ የነበረው ክርክር ያተኮረው የሶስተኛው አለም ሕዝቦች ኩሬን በአግባቡ መጠቀም ከተሳናቸውና የወባ ትንኝን በሌላ መንገድ ማጥፋት ካልቻሉ ዲዲትን ይጠቀሙ በሚሉትና የለም ዲዲቲ በራሱ በሽታ አምጪ ስለሆነ መጠቀም የለባቸውም በሚሉት ተመራማሪዎች መካከል ነበር። በሌላ አነጋገር ጥያቄው ያልታደሉት አፍሪካውያን ዲዲቲን ተጠቅመው ዛሬ ከወባ በሽታ ተርፈው ከሃያና ከሰላሳ አመት በኋላ በዲዲቲ- ወለድ በሽታ ቢሞቱ ይሻላል ወይስ ቆይተው ለማይድን የዲዲቲ- ወለድ ሕመም ከሚጋለጡ ዛሬውኑ የወባ ሰለባ ሆነው ቢለይላቸው ይሻላል የሚል "ከሁለት ሰይጣኖች የትኛውን ትመርጣለህ" አይነት ጥያቄ ነበር። የኔ ሐሳብ ደግሞ በአረመኔ ፍጡራን የተዋቀሩት የአፍሪካ አገዛዞች ከተወገዱና ሕዝቡ የስሜት ሕዋሳቱንና አእምሮውን ያለምንም ስጋት መጠቀም ከቻለ የአፍሪካ ሕዝብ ዲዲቲ ከመጠቀምም ሆነ በወባ ከማለቅ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊድን ይችላል የሚል ነበር።

እኛ ጦቢያውያን አገዛዝ ሰውን ፈጀው እያልን ብዙን ጊዜ ድምፅ የምናሰማውና ሰልፍ የምንወጣው ገዥዎች ቃታ እየሳቡ የዜጎችን ጭንቅላትና ደረት ሲበረቅሱት ስናይ አለዚያም ስብእናቸውን ተገፈው ከመኖር ይልቅ ሰው ሆነው ለመሞት የቆረጡ ጀግኖችን ተወልደው በአደጉበት ምድር ከርቸሌ ከተው ማሰቃየታቸውን ስንገነዘብ ነው። እኔ ግን በዚህ በሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን መከላከልና መዳን በሚችሉት እንደ ወባ፣ ተስቦ፣ ሳንባ ነቀርሳ፣ ጠኔ በመሳሰሉት በሽታዎች የሚያልቀው ሕዝብም ግፈኛ አገዛዝ ወይም ሥርዓት እንደገደለው መቆጠር አለበት ባይ ነኝ። በተመሳሳይ መንገድ ፕሮፌሰር ሁዋይቶን የቆቃን እልቂት መንስኤ ማይክሮሲስቲስ አልጌ ሳይሆን አይቀርም ቢሉም እኔ በበኩሌ ግን እልቂቱን ፈጻሚዎች የራሳቸውን ጥቅም እያሳደዱ ቆቃ አካባቢ ግብር ከፋይ ዜጋ መኖሩን የረሱ አረመኔ ፍጡራን ናቸው ባይ ነኝ። እንደሚታወቀው ይህ አይነት እልቂት በምእራቡ አለም የተከሰተ ቢሆን ኖሮ ይህኔ ስንቶች በፍርድ ቤት ሲንቀጠቀጡ በታዩ ነበር። ስለዚህ እንደኔ እንደኔ  ፀረ-ስብእና ወንጀል (crime against humanity) የሚያካትተው በባሩድ ሕዝብ መጨርገድን ብቻ ሳይሆን አካባቢን መበከልን ወይም የተበከለ አካባቢ ሰዎችን ሲቀስፍ ሐላፊነትን ረስቶ በሕዝብ ንብረት የግል ኑሮን ማደላደልን ወይም በእንዝላልነት መመልከትንም ጭምር ነው። አመሰግናለሁ።


*ዋቢ (Accessed on 4/12/2009)*

1. *BBC News: **Water pipe sparks Ethiopian conflict http://news.bbc.co.uk/2/hi/africa/7929104.stm***
2. *People and Power, The Green Lake, Aljezera http://www.youtube.com/watch?v=eUqgUR4qI98 (part 1) http://www.youtube.com/watch?v=rTUEjL8OhII (part 2)*
3. *Cohn et al; DDT and Breast Cancer; Environ Health Perspect. 2007 October; 115(10): 1406–1414.*
4. *ጦቢያውያንና ጤንነታቸው http://www.abbaymedia.com/pdf/Amharic/Tenna.pdf*
5. *ይድረስ ለእኛ* www.quatero.net/meta/yidres.pdf
6. *ለመሆኑ አሁን ኢትዮጵያ አገር ናት ወይ http://addisvoice.com/amh/ager3.pdf*